# ሁላችንም የተንቦቀቦቅን በቅቧቃዎች?

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

እውቀት የሚለው ስም አወቀ ከሚለው ግስ እንደዚሁም ማወቅ ከሚለው ርዕስ ጋር የተሳሰረ ነው። በኔ አመለካከት ማወቅ ከመገንዘብና ከመረዳትም በላይ ነው። ማወቅ አንድን ነገር በሚጋባ አጥንቶና ተገንዝቦ ቢቻል የተገነዘቡትን ነገር በምርምርና በልምድ ማዳበር አለለዚያም ያንን ነገር በሚገባ አንከረባብሶ መጠቀም መቻልን ያመለክታል። አንድ አዋቂ በሆነ ነገር ላይ እውቀት አለው ሲባል በዚያ የእውቀት ውቂያኖስ ውስጥ እንደ አሳ የመዋኘት፣ እንደ ኖህ መርከብም ነፋስና ውሽንፍርን ተቋቁሞ የመሻገር ችሎታ ያለው ሊቅ ነው ማለት ነው። ጠለቅ ያለ እውቀትም እንደ ጥቅምት ማር ዳኅስ ብሎ የሚፈሰው ከእንደዚህ አይነት ስፍራ ሲመነጭ ነው። በልጅነት ዘመኔ አንድ ሊቀ-ጠበብት "ቅኔ እንደ በልጅግ (እንግዳ ለሆነባችሁ በልጅግ የጠመንጃ አይነት ነው) ውልቅልቅ አድርገው ፈተው መገጣጠም ይችላሉ!" ሲባል እሰማ ነበር።

በ19ኛው ክፍለ-ዘመን ስፔንሰር የተባለ ፈላስፋ "የእውቀት ትንሹ ያልተጣመረ እውቀት ነው!" ብሎ ነበር። (1) ያ ዘመን አዝጋሚ ለውጥ (ኢቮሉሽን) የሚባለው አመለካከት እየገነነ የመጣበት በሌላ በኩል ደግሞ ይኸንን የሚቃወሙ ሽንጣቸው ገትረው የሚከራከሩበት ዘመን ነበር። ደስ የሚል፣ የሚያረካ፣ እንኳን ለሰው ልጅ ለፍጥረታት ሁሉ የሚበጅ የወንበር ሳይሆን የልቡና ክርክር! ከብዙ አመታት የአእምሮ ፍጭት በኋላ ከዳርዊን ቀደም ብሎ አዝጋሚ ለውጥን ይደግፍ የነበረው ስፔንሰር ሁለቱን ጎራዎች ለማቀራረብ ጣረ። እንዲህም አለ። " ሳይንስና ሃይማኖት የማይታረቁ ነገሮች አይደሉምና እናስታርቃቸው!" ስፔንሰር ሁለቱን ማስታረቅ የሚቻለውም ሳይንስ ሃይማኖትን ሲያውቅ ሃይማኖትም በበኩሉ ሳይንስን ሲያውቅ መሆኑን አስገነዘበ። ትልቅ እውቀት የእውቀቶች ጥምረት፤ ትንሽ እውቀትም ብቻውን ቆሞ የቀረ እውቀት መሆኑን አስተማረ።

እንኳን አገርን የሚያህል ነገር ደሳሳ ጎጆ እንኳን ሲሰራ የብዙ ጥበቦች ጥምረት ያስፈልጋል። አዎ እንኳን ቤት ዳስንም ለመስራት የብዙ እውቀቶች ጥምረት፤ ትልቅ እውቀት ያስፈልጋል። ጣራ የመስራት፣ ምሰሶ የመለካት፤ ገመድ የመሸረብ፤ የመምረግ፤ የመለሰን ወዘተ ችሎታ ያላቸው ጥበበኞች ጥምረት ያስፈልጋል። እንደ አለመታደል ሆኖ በአፍሪካ በተለይም በጦቢያ እውቀት ተገዳ እንድትመነጭ የምትፈለገው ግን እነሱ ቤተ-መንግስት ከሚሉት ቤተ-ሰይጣን ውስጥ ከተጎለተ ወንበር ከሚባል ዳኑ ግን የድብዳብ ያህል ክብር ከሌለው መቀመጫ ነው። "እዚህ ወንበር ላይ የሚቀመጥ ሰው ሁሉን ነገር አውቆ መገኘት አለበት የሚል የመለኮት ትእዛዝ" ያለ ይመስል አንዱንም ሳያውቁ ሁሉን አዋቂ መስለው ቀደም ቀደም ማለት፥ ሲናገሩም ጠረጴዛ መውቀር ያበዛሉ። ምክር እየጠየቁ በመጠቀም ፋንታ ባለሙያን እንደጠላት እያዩ ከማፈንም አልፎ እያሳደዱ ማባረር ሲያስፈልግም በሰበብ አስባቡ መግደልን ያዘወትራሉ። እርግጥ ነው ይህ ቤተ-ሰይጣን የሚገኝ ወንበር ለሽርሽር ወጥቶ ሰፌ ሜዳ ሲያይ "እዚህ ላይ ባቄላ ዝሩ!" ይላል! ድንጋይና ስሚንቶ ዩኒቨርሲቲ ይሆን ይመስል ጠጠርና ድንጋይ ሲያይ "እዚህ ቦታ የኮሌጅ ግንብ ገንቡ!" ይላል። አዎ እዚያ ወንበር ላይ የሚቀመጥ ጎሾ ሁሉ ወዲያው ሱሪው እንኳን ሳይተሻሽ "ሊቅ" ሆኖ ያርፈውና "ሁሉን አውቃለሁ፣ ከኔ ወዲያ ላሳር፣ እኔን የጠላ የማርያም ጠላት!" ማለት ይጀመራል። በእውነቱ በኛ አገር ሕዝብ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርም ትልቅ ፈተና ገጥሞታል። እንደ ራሱ እንደ አምላክ "ሁሉን አውቃለሁ፣ ቀናተኛ አምላክ ነኝና ከኔ በስተቀር ሌላ አታምልኩ፣ እኔ ዘላለማዊ ነኝ" የሚል አደገኛ ተቀናቃኝ ተፈጥሮበታልና።

አውሮጳና ሌሎችም ምእራባውያን አገሮች ምርምር፣ ክርክር፣ ፉክክር፣ የጦፈባቸው ዘርፈ ብዙ መድረኮች እየፈጠሩ፣ አእምሮን ጅምናስቲክ እያሰሩና እያዳበሩ አሁን ከደረሱበት ደረጃ ደርሰዋል። ምእራባዊያን አገሮችን የበሩና ያሸበረቁ እንዲሆኑ ያደረጋቸው በመልካም አስተዳደር ፈቃድ ሲያንጥፉት የኖሩት ሰፌ የእውቀት ስጋጃ እንጅ የሕዝቡ የቆዳ ንጣት አይመስለኝም። በአንጻሩም የእኛን አፍሪካውያንን ድቅድቅ ያልን ጨለማ ያስመሰለን በአልጠግብ-ባይ አገረ ገዥዎች ሲደረት የኖረ አሁንም በመዘርጋት ላይ ያለ የድንቁርና መጋረጃ እንጅ የቆዳችን ጥቁረት አይመስለኝም። እንዲያውም ብርሃን እጅግ ሲበዛስ ለማየት የሚስቸግረውና የማይታየው ነጭ ነገር ነው። አዎ ብርጭጭ ያለ ነገር ብርሃን ሲደምቅ ያጥበረብራል። ከቀለም ይልቅ ያላወቁት ነገር ሁሉ ጨለማ ነው። ጨለማ ደግሞ ያስፈራል። የሚፈሩትን ነገር ደግሞ ወይ ይሸሹታል፣ አለዚያም ለማጣፋት ይታገሉታል፤ ወይም ደግሞ እንደ ባህር ቄጠማ እየተንቀጠቀጡ ይገዙለታል።

በአፍሪካ ብዙውን ጊዜ ሬሳ ረግጠው ወንበር ላይ ቁጢጥ የሚሉ ገዥዎችና እውቀት አይተዋወቁም። እውቀት ብዙውን ጊዜ እንደ ሻማ፣ ጧፍና ኩራዝ በመሳሰሉ የብርሃን ጨረሮች ትመሰላለች። ዳኑ ግን ካላዩት ወይም ለማየት ፈቃደኛ ካልሆኑ ራሱ የብርሃን ጨረርም ቢሆን ጨለማ ነው። "በከንቱ የቅዱሳንን ስም አትጥራ!" አትበሉኝ እንጅ እሙ-ብርሃንን! ካላዩት ብርሃንም

ቢሆን ያስፈራል። አዎ ያላወቁት ነገር ሁሉ ደረጃው ይለያይ እንጅ በፍርሃት አስርዶ እንደ ቆቅ ያስደነብራል። ልጅ ሳለሁ በአንድ ክረምት ምሽት ወቅት ወደ ዘመድ ቤት ስሄድ አንድ ጥቁር ነገር ከሩቅ ታየችኝ። እየቀረብኩ በሄድኩ ቁጥር ትንሿ ነገር ወደ ግዙፍ አካል እየተቀየረች መጣች። በጣም እየተጠጋሁ ሲሄድም  የሚንቀሳቀስ እግር ያለው ነገር መሰለኝና አረፈው።  እየቆየሁ ስሄድ እንዲያውም የሰላ ጥርስ ያለው  ባለ ብዙ ጥፍር አውሬ መለሰለኝና ቁጭ አለ። ወዲያው ፊቴን አዙሬ ነፌሴ አውጭኝ ሩጫ ሮጥኩና ወደ ቤታችን ተመለስኩ። (በነገራችን ላይ ይህችን ከማንም ደብቄያት የኖርኳትን ጉዴን ለሰው አታካፍሏት።)  በነጋታው ተነስቼ ማታ ያስደነበረችኝ ነገር ምን እንደነበረች ለማረጋገጥ ተመልሼ ስሄድ በቅርቡ የተተከለች የባህር ዛፍ ችግኝ ሆና አገኘኋትና አያፍሩት ሐፍረት አፈርኩ።  "ምን አይነቱ ቦቅቧቃ ነው!" ልትሉ እንደምትችሉ እገምታለሁ። ተሽላችሁ ከተገኛችሁ ይህን ብቻ ሳይሆን ሌላ ሌላም ብትሉኝ ይገባል!

አብዛኛው የአፍሪካ በተለይም ደግሞ የጦቢያ ገዥዎች እውቀትን እንደዚያች በጨለማ እንደታየችኝ የባህር ዛፍ ችግኝ የሚያይዋት ይመስለኛል። እውቀት በአይነ-ህሊናቸው በመጣችባቸው ቁጥር ነፍስ ያላት፣ ቦጫጭራ፣ ነክሳ ደም በደም አርጋ የምትገል ተንቀሳቃሽ አውሬ ሆና ትታያቸዋለች ብዬ አስባለሁ። ነብር ሆና ቆዳቸውን ስትቧጭራቸው፣ አንበሳ ሆና አዙሮ ማየት የተሳነውን ማጅራታቸን ስትዘነችራቸው፣ ጅብ ሆና ታፋቸውን ስትገነጥላቸው የሚታያቸው ይመስለኛል። አዎ አይናማዋ እውቀት ለነሱ ጨለማ መስላ ስለምትታያቸው በጣም ይፈሯታል። ከፍርሃታቸው የተነሳም የምትውጥ አውሬ እየመሰለቻቻቸው ደመ-ነፍሳዊ አጸፋ በእውቀት ላይ ማውረዱን ቀጥለዋል። በእውቀት መገዛትን አልመረጡም።  ከእውቀት ሸሽቶ ማምለጥንም አልወደዱም። ከአልጠፋች እንደማትተኛላቸው ስለሚገባቸው አንቀው ሲጥ ሊያደርጓት ጉረሮዋን አንቀው ይዘዋታል። አብዛኛው ሕዝብ እንደሚገነዘበው እውቀትን ለማጥፋት ሽንጣቸውን ገትረው ሲታገሉ ይታያሉ። እንቅልፍም ያጡ ይመስላሉ። ሥርዓተ-ትምህርቱን አሽመድምደዋል። እውቀትም ልምድም ያላቸውን ምሁራን በመጥረጊያ ጠራርገው አባረዋል፤ አስረዋል። የተገደሉም አሉ። ታሪክን ፍቀዋል። ሕዝቡ እውቀቱን ልምዱን እንዳይካፈል በትምህርት ተቋማትም ሆነ በሰፈር ውይይት ከልክለዋል። በየሰው ደጅ፣ መስሪያ ቤት ጆሮ ጠቢ አስቀምጠዋል። ከዚያም አልፈው በዚህም በዚያም ብለው ያሰደዱት ሕዝብ በተሰደደበት አገር እንዳይወያይና  ስለ አገሩ ግንዛቤውን እንዳያሰፋ የሚሰነጣጥቅ፣ የሚከፋፍልና የሚያናክስ መርዝ እየረጩ እንኳን ከስብሰባ ቦታ ከቤተ-ክርስቲያን ሳይቀር ይበታትኑታል።

በምእራቡ አለም በየቀኑ ስለማርስና ሌሎችም ፕላኔቶች ዜና ሲዘገብ የጦቢያ ጋዜጠኛ ስለ ዶሮ-ማነቂያ፣ ስለ ደንቢ ዶሎ፣ ስለ አደባባይ እየሱስ፣ ስለቀብሪ ደሀር፣ ስለ አላፋ ጣቁሳ ወዘተ ዘገብክ ተብሎ ከወስላታ ፍርድ ቤት ተገትሮ ይውላል፤ አይቀጡ ቅጣትም ይቀጣል።  ከዚያም አልፎ ይታሰራል፤ ወህኒ ቤት በስብሶ እንዲሞት አለበለዚያም እንዲሰደድ ይደረጋል። ጋዜጦች ወይም መጻሕፍት እንዳይታተሙ ማሳተሚያ ዋጋውን ያንሩታል። ጸሐፊ ምን መጻፍ ዘፋኝም ምን ማቀንቀን እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ደንብ ያወጡለታል። በሌላ አነጋገር የአእምሮን ፍሬ ቀጥቅጠው ሰልበውታል። የአቶምን ኤሌክትሮን ለማየት ሲጥር የሚውልን የፊዚክስ ምሁር አይነ-ስውር እንኳን የማይስተውን የባቱን ተራራ ለምን አየህ፣ ስለባሌስ ለምን አወራህ ተብሎ ከስራ ይባረራል። ሕዝቡ ጤነኛ ጆሮ እያለው ደንቆሮ፣ ብሩህ አይን እያለው እውር ሆኖ እንዲኖር ተደርጓል።  በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ራዲዮ እየታፈነበት፣ ስልክ እየተጠለፈበት፣ ኢንተርኔት አገልግሎች እየተነፈገው ያለውም ራሱ በገበረው ግብር  በተገዛ መዝጊያና ቁልፍ ችንክር አርጎ እየተቆለፈበት ይኖራል። ታዲያ ይህ ሁሉ የእውቀት በር ጥርቅም ተደርጎ ተዘግቶ ዝናብ እንኳን ባጠረበት ዘመን እውቀት ከሰማይ እንዲዘንብለት የጦቢያ ሕዝብ አንገቱን ወደ ሰማይ አንጋጦ መጠባበቅ አለበት ማለት ይሆን?  ሰው ካልሰማ፣ ካላነበበ፣ ካልጻፈ፣ ካልተነጋገረ፣ ሐሳብ ለሐሳብ ካልተለዋወጠ እንዴት ተብሎ የችግርና የበሽታ መላቀቂያ ዘመናዊ መንገድ መፈለግ ይቻላል? ይገርማል! በደንብ ላጤነው እውቀትን መፍራትስ የጨለማን ችግኝ ከመፍራትም ይብሳል። አዎ እውቀትን መፍራትስ ኮቢ ቀለም ለመትፋት ቆቧን አውልቃ ኩንቢዋን ወረቀት ላይ በተከለች ቁጥር ሱሪው የሚረጥብ ቡቅቡቅ ያለ ቦቅቧቃ ያደርጋል።

የሚገርመው ደግሞ የእኛ በመገዛት ላይ ያለነው አፍሪካውያን በተለይም ደግሞ የአንዳንድ ጦቢያውያን የጀግንነትና የአርቆ አሳቢነት ግንዛቤ ጉዳይ ነው። እንደዚህ ያሉትን አሻንጉሊት ገዥዎች የእስስትነት ባህሪና ውሸትን በውሸት ሳሙና እያጠቡ አሙለጭልጮ መሹለክለክ እንደ ጉብዝና፣ እንደ ጥልቅ አሳቢነት፣ እንደ ጀግንነት እየቆጠርን የምናደንቅ አለን ። ያሳዝናል! በእውነት ጀግንነት ጠላት በቀመረው አጀንዳ እየተመሩ ስንት ሺህ ዘመን የተገነባን አገር መናድ ከሆነ፣ አርቆ አሳቢነትና ጉብዝና ህሊናን ከስሩ መንግሎ ገፋፎ መጣል ከሆነ፣ ክህደትን፣ ቅጥፈትን፣ የእለት ከእለት መመሪያ ማድረግ ከሆነ፣ በሌሎች የምሳር እጀታ ውስጥ ገብቶ የራስን ግንድ ቆራርጦ መጣል ከሆነ፣ አለም አንድ እየሆነ በመጣበጥ ዘመን የክልል ችካል ሲተክሉ መዋል ከሆነ፣ እውቀት እንኳን እንዳትንሰራራ ያለችዋም እንድትጠፋ ላይ-ታች ሲሉ መዋል ከሆነ፤ ጀግንነትም ሆነ ጥልቅ አሳቢነት እንደገና መብራራት(define መሆን) አለባቸው ብየ እገምታለሁ።

በጎ በማያስቡ ባእዳን ትከሻ ላይ እሽኮኮ ተይዞ በራስ ሕዝብ ላይ ቃታ መሳብ፣ ማንኛውም የእውቀት ማግኛ መንገድ ሕዝብን መንፈግ፣ ሕዝብን ችግርና በሽታን ታቅፎ እንዲኖር ማድረግ፤ መቅጠፍ፣ መክዳትና ስግብግብነት የእርግማን እንጅ የጥልቅ አሳቢነትም ሆነ የጀግንነት ምልክቶች ሊሆኑ አይችሉም። ጥልቅ ወይም አርቆ አሳቢነት አያት ቅድመ አያቶች የተሰውበትን ጠቃሚ መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ እሴት መጠበቅ፣ የአሁኑን ትውልድም ከችጋር፣ ከበሽታ፣ ከማይምነትና ከሌሎችም ከሰው

በታች ከሚያውሉ የኅብረተሰብ ጠንቆች ማላቀቅና መከላከል፣ እየተከታተለ ለሚመጣው ለወደፊቱ ትውልድም የተመቻቸ እድል ማቆየት፣ ከራስ ሕዝብና ከቅየም አልፎ ባጠቃላይ ለሰው ልጅ ሁሉ፣ ለሌሎች ፍጡራን፣ ለምድሩ፣ ለሰማዩ፤ በአጠቃላይ ለምንኖርባት አለም በጎ ነገር አበርክቶ ለማለፍ መጣር ይመስለኛል። ጀግንነት እንደዚሁ በመሰሪ የባእድ ሞግዚት ወይም ደጋፊ ግራና ቀኝ ተደግፎ፣ በግል ጥቅምና ጥላቻ ሰክሮ ሌላውን ሰው ታግሎ ማሸነፍ ወይም መጣል ሳይሆን አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ ሐይልን ከግላዊ ጥቅም አላቆ፤ ኢፍትሐዊነትንና ባርነትን አስወግዶ፤ ፍትህንና ነጻነትን ለማስፈን መጣር ነው ብዬ አስባለሁ። ጋንዲ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ኔልሰን ማንዴላ፣ አቡነ ጴጥሮስ፣ ሀዲስ አለማየሁና መስፍን ወልደ ማርያም የአርቆ አሳቢዎችና ጀግኖች ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ።  የሰሩት ስራ ሁሉ ለራሳቸው ክብር፣ ሆድና ምቾት ላለመሆኑ የዋሉበት ቦታና የኖሩት ኑሮ ይመሰክራል። (ስለ ክቡር አቶ ሀዲስ አለማየሁና ፕሮፌሰር መስፈን ወልደ ማርያም የተጻፈች የምስጋና ገጸ-በረከት ለማንበብ በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ላይ ከተጠቀሱት ዋቢዎች ውስጥ ቁጥር-2 ተጭነው ያንብቡ።)

አሁን አሁን የባንድነት ሽል እንደ እንጉዳይ ሲፈላ የጀግንነት ማህጸን ያረጠ ይመስላል እንጅ ድሮ ድሮ በጦቢያ ጀግና ከየአቅጣጫው ይወለድ ነበር። አዎን! እንደ ጎርፍ የሚፈሰውን የባእዳን መደለያ ባፍንጫችን ይውጣ እያሉ እንደ ነፃ አውጪው ሙሴ ከተራራውና ከበረሃው ተስማምተው መንግስት እንኳን በፈራረሰበት ወቅት የአባቶቻቸውን አደራ በተወጡት፣ ለተተኪው ትውልድም ያልተቆራረሰች ምድር ባስረከቡት፤ ዛሬ አጥንታቸው በሚወቅሰን እንደነ በላይ ዘለቀ፣ አበበ አረጋይ፣ አብዲሳ አጋ፣ ባልቻ አባነፍሶ፣ አያሌው ብሩ፣ ዘርዓይ ደረሰ፣ መንገሻ ጀምበሬና ሌሎችም ቁጥር ስፍር በሌላቸው አርበኞች ዘንድ ጀግንነት በሚገባ ታይቷል። የዚህ ጸሐፊ አባትም እንዳቅሙ በ10 አመቱ በጣልያን ወረራ ጊዜ በረሃና ዱር ገብቶ  አከታትሎ እየተኮሰ የሞሶሎኒን ኢፍትሐዊነትና ባርነት የማስፈን ህልም ወደ ቅዠትነት ለመቀየር በረሃ ገብቶ ለነበረው አጎቱ የሚኒሽር ጥይት በካርታ እየሰካ በማቀበል፣ ጠመንጃ በመወልወልና አንጋች በመሆን ሁለተኛውን ጥርሱን አብቅሎ ሳይጨርስ ግዳጁን የተወጣ የልጅ አርበኛ ነበር። ችግሩ ግን “ገታ ሙሽ ይወልዳል” እንዲሉ ሌላ ሳይሆን የባህርዛፍ ችግኝ ሲያይ ዞሮ የሚፈተለከውን እኔን ወልዷል።

እንግዲህ ከላይ እንደተገለጸው ብዙዎቹ የአፍሪካ ገዥዎች ጀግና ቀርቶ  ሙሉ ሰዎች (ስለ ሰው አይነት ዋቢ 3-4ን ያንብቡ) እንኳን ያልሆኑ እውቀትን የሞት ያህል የሚፈሩ፣ትናንትም ሆነ ነገ የማይታያቸው እንዲያውም ከዛሬም አሁኗ ደቂቃ ላይ በአቃጭል የተቀመጡ አሻንጉሊት የሆኑ ከንቱ ፍጡራን ናቸው። እኛም እየተንጸረጸረን የምንኖረው አካል ሳይኖራት የሰላ አቅንጣጤ ወይም ሰይፍና ጎራዴ አላት ብለው እውቀት ወደ ሕዝቡ ለመስረጽ በቃጣች ቁጥር ሆዳቸውን ባርባር የሚላቸውን ቦቅቧቃ ፍጡራንን በመፍራት ነው። የጊዜ ጉዳይ እንጅ ቡጢ እውቀትን አሸንፏት አይቀርም። በቡጢማ ቢሆን ዝሆን ፍጥረትን ሁሉ በገዛው ነበር። ታሪክም የሚነግረው ይኸንኑ ነው። አይገመግሜው ዳይኖሶር ሰውን እስከ መጨረሻው አሸንፎት ቀረ እንዴ? ታዋቂው ፈላስፋ ስፓይኖዛ “የነጻነት ሐይል እውቀት ብቻ ነው!” ብሎ ነበር። (5) እኔ እንደገባኝ ይህ ማለት እንኳን እውቀትን የሚያጠፋ ለማወቅ ያልተዘጋጀ ሰው፣ ለእውቀት በር የማይከፍት ሰውም ደከማና መንፈሱ በባርነት መቀመቅ ውስጥ እየተሰቃየ የሚኖር ከንቱ ሰው ነው ማለት ነው። ታዲያ እንግዲህ እውቀት ፍዳዋን በምታይበት በዛሬዋ ጦቢያ ማነው የባሰ ደካማ? ማነው የባሰ ባርያ? ማነው ቦቅቧቃ? በጨለማ የሚታይን ችግኝ ፈርቶ የሚሸሽ? እውቀት በውኑም በህልሙም ስታቃዠውና ስታስደነብረው ጨረሯን ለመከላከል የቻይናን ቡቱቶ እየጎተተ የእውቀት ጮራ መግቢያ ጨላጨሎውን(ቀዳዳ) ሁሉ ሲደፍን የሚውል የድንቁርና መሪ ተዋናይ? ጨለማ ውስጥ ተወርውሮ እድሜውን በመግፋት ላይ ያለ ያልታደለ ሕዝብ? ወይስ ተሰዶ (ስለ ስደት ዋቢ 6 ያንብቡ) ሌሎች ያበሩትን የእውቀት ብርሃን በማድነቅ ላይ የኔ ቢጤ ዘመናዊ ባርያ? ምናልባት ሁላችንም ቅድመ አያቶቻችን ሰማይ ቤት ሆነው የሚያዝኑብን፤ መጪው ትውልድም ጊዜውን እየጠበቀ ሲመጣ አንገቱን ደፍቶ የሚያፍርብን የሃያ-አንደኛው ክፍለ-ዘመን የተንቦቀቦቅን ቦቅቧቃዎች? አይደለሁም የሚል እጁን ያውጣ!!

### ዋቢ


1. *Hebert Spencer;  Will Durant; The story of Philosophy; 5th edition, 1933, page 265-290*
2. ከሐዋርያትና ሰማእታት ለመረከብ የከበደን ጸጋ! ለማንበብ ይህንን ይጫኑ
   http://addisvoice.com/article/Tsega.pdf http://www.quatero.net/meta/Tsega.pdf
3. *ሰው ምንድን ነው? ለማንበብ ይህንን ይጫኑ www.addisvoice.com/article/sew2.pdf*
4. *ደግነትና ክፋት ምንድን ናቸው? ለማንበብ ይህንን ይጫኑ http://addisvoice.com/article/Good.pdf or http://www.quatero.net/meta/GoodandEvil.pdf*
5. *Spinoza; Will Durnat; The story of Philospophy; 5th edition, page 128*
6. *ለምን እንሰደዳለን? ለምንስ ደኸየን? ለማንበብ ይህን ይጫኑ http://www.abbaymedia.com/pdf/Amharic/Sidet.pdf*


ሐምሌ 2000 ዓ.ም.